# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com


ቀን፣ 31,03,2016

## ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) መሻሻልና መጠናከር የሸንጎ ምክርና አስተያየት

የሆነንና የተደረገን ድርጊት በትክክል ተከታትሎ መረዳትና ማስረዳት ከአንድ ሃቀኛ የዜና ተቋም የሚጠበቅ ግዴታ ነው።አንድ የዜና ተቋም ያሰራር ድክመት ካለበት ወይም በሌላ ሃይል ፍላጎትና ትእዛዝ የሚንቀሳቀስ ከሆነ፣የሁሉንም ድምጽ በእኩል ደረጃና ወገንተኛ ባልሆነ መንገድ ካላስተናገደ የሚጠበቅበትን የሙያ ተግባርና ግዴታ ሊያሟላ አይችልም።የህብረተሰቡንም እምነት ያጣል፤እንኳንስ ልቡን ቀርቶ ጆሮውን የሚሰጠው ይጠፋል።

በአገራችን እንደሚታየውና እንደሚታወቀው የዜና አውታሮቹ የመንግሥት ልሳን በመሆን ሲያገለገሉ፣ በሥራውም ላይ የተሰማሩት ሙያተኞች የዛሉ ደመወዝ የሚከፍላቸውን የመንግሥት መልእክት ሲያስተጋቡ፣የሕዝቡን ድምጽ በመጫናቸው የአመኔታና የአክብሮት ደሃ አድርጓቸዋል።ተደናግረው ሕዝብ ሲያደናግሩ፣.በቀድሞ የካቲትና ከዚያም በኋላ በሚዲያ ዘርፉ የተሰለፉት ውሻ በበላበት ይጮሃል የሚል ትችት ሲሰነዘርባቸው የማስታወቂያ ሚኒስቴር የተባለውም የጋዜጠኞች ቀጣሪ ተቋም ውሻ በረት የሚል መጠሪያ ተሰጥቶት እንደነበረ የምናስታውሰው ብዙዎች ነን።

በዚህ እረገድ የሚታየው ድክመት ተሻሽሎ የሚዲያ መስክ ታማኝና አስተዋይ፣አስተማሪ እንዲሁም በሙያው የተሰለፉት ለእምነታቸውና ለእውነት የቆሙ ባለሙያዎች ሆነው ለማየት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመኘው ጉዳይ ነው።ያ ምኞቱ ግን በተግባር ሳይገለጽ ለብዙ ዓመት ቆይቷል።

ከአምስት ዓመታት በፊት በውጭ አገር ፣በኢትዮጵያኑ ትብብርና ጥረት የኢትዮጵያ ሳተላይት የቴለቪዥን(ኢሳት) መስመር ሲመሰረት ብዙ ኢትዮጵያውያን በደስታ ፈንድቀው የተጠየቁትን የገንዘብ እርዳታ ለመለገስ ወደኋላ አላሉም፤በውጭ አገር በመቋቋሙም በሥራው የተሰማሩት ግለሰቦች ካሉበት አካባቢ ካለው የነጻ የሚዲያ አሰራር ትምህርት ቀስመው ለሙያቸው ይሰራሉ፣ሕዝብ ያጣውን የእውነት መረጃ ያቀርባሉ የሚል ጉጉትና ተስፋ አድሮበት ነበር።

ሸንጎም እንደሌሎቹ የሚዲያ ነጻነት እንደሚያሳስባቸውና እንደሚታገሉለት ድርጅቶች በኢሳት ላይ እምነት አድሮበት ነበር።ኢሳት ሲቋቋም ጥረት ካደረጉት መካከልም አንዳንዶቹ የሸንጎ አባላት ናቸው።

ሸንጎ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አልፎ አልፎ ለህብረተሰቡ ለማሰማት የኢሳት ትብብር አልተለየውም።ለዚህም በተደጋጋሚ ምስጋናውን በቦታውና በወቅቱ ገልጿል።ይህ ማለት ግን ሸንጎ በኢሳት አሰራርና የሚዲያ አቀራረብ ሙሉ ለሙሉ የረካና ትክክለኛ የሚዲያ አሰራር የሚከተል ነው ብሎ አልደመደመም።የተሻለና በድርጅትም ሆነ በግለሰብ ፈቃድና ፍላጎት የማይሽከረከር፣ ሙሉ በሙሉ ነጻነት ያለው የሚዲያ ዘርፍ እንዲቋቋም በሚያስችለው መንገድ የድርሻውን ለማበርከት ዝግጁ ነው።

ኢሳት አልፎ አልፎ በሸንጎ ዙሪያ በሚከናወኑት ተግባሮች ላይ የተሟላና የተስተካከለ ዘገባ እንደማያቀርብ በተደጋጋሚ የታዬ ነው። ሆኖም ግን ሸንጎ ከእለት እለት ይሻሻል ይሆናል፣በውሃ ቀጠነ ከመራራቁ ተቀራርቦ ስህተቶች ታርመው የእውነተኛ ነጻ ሚዲያ አሰራር ሊከተል ይችላል የሚል እምነት ነበረው።ይሁን እንጂ አሁንም በአደባባይ የቀረበን እውነታ በመካድና በማጣመም ለአድማጩ የተዛባ ዜናና መረጃ የማቅረቡ ልማድ በመቀጠሉ ይህንን ምክርና ማብራሪያ ለማውጣት ሸንጎ ተገዷል።

ሰሞኑን ፣በማርች 26 እና 27 ቀን 2016 በዋሽንግተን ከተማ በቪዥን ኢትዮጵያ በተባለ ድርጅትና በኢሳት ተባባሪነት የተዘጋጀ የውይይት ጉባኤ ተጠርቶ ነበር።በዚህም ጉባኤ ላይ እንደ ሌሎቹ በተወካዮ አማካኝነት የሸንጎን ራዕይና የሚያካሂደውን የትግል


*Tel.* : +44 7937600756 , +1 9168486790

*E-mail* : shengo.derbiaber@gmail.com

ድርሻ የሚያብራራ ጽሁፍ አቅርቧል።ከተሰብሳቢው ለተወረወሩት ጥያቄዎችም አቅራቢው ማብራሪያ ሰጥቷል።ይህን በግልጽ የተደረገ ውይይትና አቀራረብ በቦታው የተገኘው ብቻ ሳይሆን ስብሰባውን አስመልክቶ በልዩ ልዩ ድረገጾች በወጣውና በአዲስ ድምጽ ራዲዮ በተላለፈው የዜና ስርጭት ህብረተሰቡ እንዲያውቀው ሆኗል።የሚያሳዝነው ነገር ሕዝብ በይፋ የሚያውቀውን ጉዳይ የስብሰባው አዘጋጅ አካል የሆነው ኢሳት በማግስቱ ባቀረበው ዘገባ በሸንጎ የቀረበውን ሁለገብ ትንተና ባለማቅረቡ ለዚህ የሸንጎ አስተያየትና ምክር መነሻ ሆኗል።በዘገባው የግለሰቦች ሳይቀር ሙሉ ለሙሉ የተናገሩትና ያቀረቡት ጥያቄ ሳይበጣጠስ ለመቅረብ ሲችል፣ ሸንጎ ከሃያ ደቂቃ በላይ ያቀረበው ትንታኔና ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጠው መልስ ሳይገለጽ ቀርቷል።ለምን?የቀረበውን የሸንጎ ትንታኔ ካለመረዳት ወይስ ላለማስረዳት ወይስ በሳንሱር ወይስ ከወገንተኝነት የማፈን ዝንባሌ ከመነጨ አስተሳሰብ?

ሸንጎ በኢሳትም ሆነ በኢሳት ዙሪያ ለሚንቀሳቀሱት ድርጅቶችና ግለሰቦች ቀናና ወገናዊ አመለካከትና አብሮ የመስራት ፍላጎት እንጂ ክፉ ነገር እንዲገጥማቸው አይመኝም። ብዙ ጊዜ እንዳደረገው ሁሉ ይህም ስብሰባ ሲዘጋጅ ለመሳተፍ ፍላጎቱን በተግባር ማሳየቱ የዚህ ማስረጃ ነው።ያለፈውንማ ተደጋጋሚ የማዳከም ተግባር ቢያስብማ ኑሮ በስብሰባውም ላይ ባልተካፈለ ነበር።ግን ከትናንቱ ዛሬ፣ ከዛሬም ነገ ለውጥ ይመጣ ይሆናል በሚል ቀና አስተያየት የስብሰባውን ጥሪ በአክብሮት እጁን ዘርግቶ ተቀብሎ በቦታው ላይ ተገኝቷል።በስብሰባው ላይ የአጠቃላዩን የተቃዋሚ ጎራ ድክመት መጠቆሙ የተሻለና ለድል የሚያበቃ ትግል እንዲደረግ ከመፈለግ አኳያ ሲሆን ይህንንም ትችት ሲያቀርብ በኢሳት የሚዲያ ተቋም ላይ የሚታየው ድክመቱ ተወግዶ ጠንካራና አስተማማኝ፤አንድ ድርጅት የሚያሽከረክረው ንብረት ሳይሆን እውነተኛ አማራጭ ነጻ የሕዝብ ሚዲያ ተቋም እንዲሆን፣ሰራተኞቹም ለሙያቸው ያደሩና የተከበሩ እንዲሆኑ በመመኘት ነው።ይህን ወገናዊና ገንቢ ትችት ሲያቀርብ ለማጋለጥና ለመክሰስ አይደለም፤ድክመት አለና ይስተካከል ለማለት ነው።

የሸንጎን መልእክት ብቻ አሰራጩ የሚልም ራስ ወዳድነት የለውም፣የተመዛዘነ አቀራረብና አሰራር ይኑር ነው።ይህ ደግሞ ለራሱ ለኢሳት ይጠቅመዋል እንጂ አይጎዳውም።ኢሳት ተጠቀመ ማለትም ሸንጎ ተጠቀመ፣በአጠቃላይ ዲሞክራሲና ነጻና እውነተኛ ሚዲያ የናፈቀው ወገን ተጠቀመ ማለት ነው።ጠንካራና ነጻ የሚዲያ ዘርፍ ለመሆን ኢሳት ከፈለገና በተግባርም ካሳዬ ሸንጎ ከጎኑ ይቆማል።

በየቀኑ ቤት ካልተጠረገ የቁሻሻ አቀበት መፍጠሩ አይቀርምና ተቋሙ በህወሃት/ኢህአዴግ ለጥቃት ለመጋለጥ በር እንዳይከፍት ብሎም አድማጭ እንዳያጣ ለማድረግና ለመታደግ መምከርና መጣር የሃቀኛ ወዳጅና ዘመድ ተግባር ስለሆነ ገንቢ ምክርና ትችት ለመሰንዘር ሸንጎ አይታክትም።አንድ ዓይን ይጥፋ አይባልም ግን በዓይኑ ውስጥ የተጠራቀመው ሊያጠፋው የሚችለውን ጉድፍ ማሶገዱ የእውነተኛ ወዳጅ ሥራ ነው።ስህተት እያዩ በዝምታ ማለፍ ወይም በጭፍኑ መደገፍ የመቃብር ጉድጓድ እንደመቆፈር ይቆጠራል።እሳት ከማህበረሰቡ የገንዘብ እርዳታ ብቻ ለመሰብሰብ ከሚያደርገው ጥረት ጎን ለጎን ገንቢ ሃሳቦችንም ለመሰብሰብ መነሳት አለበት።

በመጨረሻው ኢሳት ባለፉት ጊዜያቶች በሸንጎ ዙሪያ ያለውን የተዛባ አስተያየትና ግንኙነት አስተካክሎ እንደ አንድ ለለውጥ የተሰለፈ የዴሞክራቲክ ስብስብ ፣ለውጭ ሃይሎች ያላጎበደደና የማያጎበድድ፣ለአንዲት ዴሞክራቲክ አገር፣ለሕግ የበላይነት፣ከአድልኦ ለጸዳች፣ዜጋ ተከብሮና ተከባብሮ ለሚኖርባት፣ከዘረኛና ከአምባ ገነን ብሎም ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ነጻ ለሆነች ኢትዮጵያ የሚታገል መሆኑን እንዲያውቅለትና እውነተኛ ገጹን ለአዳማጮቹ እንዲያሳውቅ ይጠይቃል።ሕብረተሰቡም ትክክለኛውን የሸንጎ ገጽ የማወቅና የመረዳት መብት አለው።ያንን ለማድረግ የሚሳነው የዜና አውታር የሕብረተሰቡን መብት እንደመካድ ይቆጠርበታል።

የእሰጥ አገባ አታካሮ እንዳይነሳ በማለት ወዳለፉት ድክመቶች ለመግባት ሸንጎ ፍላጎት የለውም።ጊዜውን በታላቁ አገር አድን ሥራ ላይ ማዋል እንዳለበት ይገነዘባል።

ሸንጎ ለተሻለ ግንኙነትና ትብብር ምን ጊዜም ዝግጁ ነው፣

ለተሻለች አገር የተሻለ የሚዲያ ተቋም አስፈላጊ ነው።

*Tel.* : +44 7937600756 , +1 9168486790

*E-mail* : **shengo.derbiaber@gmail.com**